ጫጩት ፍለጋ ለንግሥና

ቤተልሔም ውስጥ ባህር ዳርቻ አካባቢ አንድ የእንቁላል ነጋዴ የመርከብ መውጫ በር ላይ ከአንድ ተቆጣጣሪ ወታደር ጋር ይጣላል። የጥላቸው መነሻ የሆነው ደግሞ እንቁላል ነጋዴው በእጁ የያዘው ጫጩት ነበር። ነጋዴው ይሄ ጫጩት ይዟቸው ከነበሩት እንቁላሎች መሃል አንዱ እንደሆነ እና እጁ ላይ ተፈልፍሎ እንደሆነ ቢያስረዳውም ቢሞግትም ወታደሩ ግን የለም ስትመጣ ይዘ የገባኸውን አይቻለው ያስመዘገብከውም እንቁላል እንጂ ዶሮ አይደለም ይመልሳል። ነጋዴው የያዝኩት ጫጩት እንጂ ዶሮ አይደለም ቢለውም ሃሳቡን ስላልተቀበለው መርከቡ ከመነሳቱ በፊት መኖሪያው ከሩቅ ሀገር ስለነበር መልካም እሺ መጣሁ ብሎ ጫጩቱን ከአንድ ስፍራ አድርጎት ጫጩቱ ባይሰማውም እንደሚመለስ ምሎለት (የዋህ ነጋዴ) በችኮላ ወደ መርከብ ይመለሳል የመርከቡ ተቆጣጣሪ ወታደር ያገኘው በደንብ ከፈተሸው በኃላ እንዲሄድ ይፈቅድለታል።

ከእንቁላሎቹ መሃል አንዱ መፈልፈሉ እጅግ አስገርሞታል በሃሳብ ይብሰለሰላል ጥቂት እንደተጓዙ የመርከቡ ተቆጣጣሪ ወታደር ወደ ነጋዴው ቀርቦ ቀድሞ ስለነበረው ነገር ይቅርታ ጠይቆት እጁ ላይ ካሉት ከቀሩት እንቁላሎችም ጥቂት ይገዛዋል። ነጋዴው አሁንም በሃሳብ መዓበል ከመርከብ ላይ ጋር ሳይሆን ከተፈለፈለው እንቁላል ላይ ይዋልላል ዲናሩን ቢቀበል እና እንቁላሉን ለተቆጣጣሪው ቢሰጠውም ልቡ ጫጩቱ ላይ ነው አወጣ አወረደ "እንዴት ሊሆን ቻለ?" አለ ነጋዴው። አናገርከኝ አለው ተቆጣጣራው። አልመለሰለትም። ከመኖሪያው ደረሰ ከቤቱ ገባ እንቁላሉን አስቀምጦ ያብሰለሰል ጀመር ልጆቹን አላናገራቸውም ግራ ገብታቸዋለው ሚምን እንደሆነ ሊያውቁ አልቻሉም መሸ ወደአልጋው ወጣ ለመተኛት ሞከረ መልሶ ወረደ ጸሎት አደረሰ ተመልሶ ወደአልጋው ወጣ ለሊቱን ሙሉ እንቅልፉን አጣ ወደቀኝ ወደግራ በደረቱ በጀርባው ለመተኛት ቢሞክር መተኛት አቃተው እንቁላሉን ተሸክሞ የት የት እንዳረፈ እያሰላሰለ ነው ለአንድ ጫጩት ይሄንን ያህል መጨነቁ ለእሱም አልገባውም ሃሳብን ሊተወው ሞከረ ሞካከረ ግን አልቻለም።

 እኩለ ለሊት ላይ አስታወሰ። ሳይተኛ ባነነ "አዎን ትዝ አለኝ አስታወስኩ ያቺ ምስኪን ደሀ መበለት ሴት" አለ። ሁኔታዋን አስታወሰው ጠርታው በአንድ ሳንቲም በሚያክሉ ሁለት ናስ ግዛኝ ዋጋህን ከአምላክ ታገኘዋለህ ያለቸውን አስታወሰ። ሁኔታዋ አኳኖኗ ስለሳዘነው ሳያቅማማ ሳንቲሙን በእጇ ሰቷት ሊጠይቃት ሲዞር ግን እንዳጣት ትዝ አለው። ለሊቱ አልነጋ አለው ምሽቱ ረዘመበት ያቺን ሴት ለማግኘት ከቀሬና ማልዶ ተነሳ ልጆቹን አሌክስንድሮስ ና ሩፎስን በደንብ ሳይሰናበታቸው ምክንያቱንም ሳይነግራቸው ተለያቸው በመርከብ ተሳፍሮ ሄዶ ለመፈለግ ጉዞ ጀመረ።

ከቤተልሔም እንደደረሰ ከተማዋን ሁሉ አካለለ መበለቷን ሴት ግን ማግኘት አቃተው በመጨረሻም ከጸሎት ቤት ጸሎት አድርሶ ጨርሶ ተቀምጦ ሳለ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሲያወራ ሰማ " እውነት እላችኋለሁ፥ ይህች ድሀ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች፤"

የሉቃስ ወንጌል 21:3

መበለት የሚለው ቃል ከጆሮው ገባ ዞሮ ሲያያት ያቺ ምስኪን መበለት ሴት ናት። ከጸሎት ቤቱ ተንደርድሮ ሄዶ አናገራት አወቅሺኝ አላት። ሁኔታዋ እንዳላስታወሰችው ሲሆንበት ጊዜ ትላንት እና እንቁላል የገዛሁሽ ነጋዴ ነኝ አላት። አንገቷን ሰብራ "ጌታዬ ትላንት የሰጠኸኝን ሳንቲም ከመዝገብ ጥየዋለሁ ይቅርታ ሌላ የምከፍልህ ምንም የለኝም እኔ ምስኪን ሴት ነኝ" አለችው። አባባሏ ውስጡን ረበሸው ምስኪንነቷ ለአምላኳ ያላት ፍቅር እና የእምነቷ ፍጹምነት አስገረመው። ለዛ አይደለም ስለጫጩቱ ልጠይቅሽ ፈልጌ ነው ማለቴ ስለእንቁላሉ። "የማይታመን ነው ሰውዬው ያሉኝ ነገር ልክ ነበር ማለት ነው" አለች ፊቷ በደስታ ተሞሎቶ መበለቷ። "የቱ ሰውዬ"

ነጋዴው ጠየቃት። መበለቷ በአርምሞ ወደአንድ ጥግ ሄዳ ተቀመጠች ነጋዴው ተከተላት።

ጥቂት ዝምታ ከሰፈነ በኃላ "የቱ ሰውዬ" መልሶ ጠየቃት። 'ለእኔ እንቁላሉን የሰጠኝ ሰውዬ። ትልቅ ሸበታም ነው በእየሩሳሌም እንደሱ ያረጀ ሰው አላየሁ እንቁላሉን የሰጠኝ ዕለት የንስሃ ሚስጢር በዚህ ይታወቃል መማሪያ ማንቂያ ይሆናል።' ነጋዴው የምታወራው አስገርሞት በተመስጦ ይሰማታል። መበለቷ 'ይሄ የክህደት መመለሻ የንስሃ ማስታወሻ ነው እናም ቀይ ከላይ ለታጠቀ ነገ በዚህ ለሚያልፍ ሰው ስጪው በምላሹም አንድ ሳንቲም ሁለት ናስ ተቀበይው።' ብሎኝ ነበር። ነጋዴው ታዲያ ለዛ ነበር ከእኔ አንድ ሳንቲም ሁለት ናስ የተቀበልሺኝ። መበለቷ በአንገቷ በአውንታ መለሰችለት። ነጋዴው ይገርማል እና አንቺ ዛሬ እንዴት ወደዚህ ልትመጪ ቻልሽ። መበለቷ "ከአንተ የተቀበልኩትን አንድ ሳንቲም ሁለት ናስ ከጌታዬ ፊት ትዳሬን ያለኝን ሁሉንም ነገሬን ከጌታዬ ፊት ለመጣል" አለችው። አሰብ አድርጎ ትዳሬ ብሎ ተመልሶ ሲያያት አጠገቡ አጣት።

ስለዶሮው እጅግ ጉጉት አድሮበት። ይፈልገው ዘንድ መንገድ ከመጀመሩ በፊት ጌታዬ ማንን ነው ያለችው አይ ቤተልሔም ሚስጥርሽ ብዙ የሆነብሽ ከተማ አለና ፊቱን ሲያዞር አንድ በግርማ እና በውበቱ የሚያስፈራ ሰው ከጾሎት ስፍራ እያስተማረ አየው። ምንአልባት እሱን ይሆናል ብሎ ጫጩቱን ፍለጋ ጀመር። ጫጩቱን ፍለጋ ብዙ ለፉ ብዙ ደከመ። የጫጩቱ ሚስጢር እስኪገለጥለት ድረስ ያገኘውን ይበላ ጀመር ምግብ እስከማጣት ለፉ ለእሱ ክፉ ጊዜ ሆነበት ይህ ሰው ሙዳ ይበላ ማር ይጠጣ የነበረ የከበረ ነጋዴ ቢሆንም አሳ እና ቂጣም በልቶ ያሳለፈበት ጊዜም ነበር አሳውን እና ቁጣውን የበላ ጊዜ አቤት የቤተልሔም አሳ አቤት የቤተልሔም ቂጣ ከማጥገቡ ጠዓሙ ብሎ በቤተልሔም ሰዎች እጅግ ቀንቶ ነበር። ጊዜ ጊዜን እየወለደ ቀን ሳምንትን ሳምንት ወራትን አስቆጠረ እንደቤተልሔም ተወላጅ ራሱን አየ። አሁንም ዶሮውን ፍለጋ ይለፋል።

አንድ ቀን በቤተ መቅደስ ገብቶ ጸልዮ ሲወጣ ረብሻ ውጪ ላይ ሲፈጠር ተመለከተ አንድ ሰው በአስራ ሁለት ሰዎች ተከቦ አየ ያ የሚረብሸውን ሰው ከአሁን ቀደም የሚያውቀው የሚያውቀው መሰለው ከየት እንደሆነ ግን ግራ ገባው። ይህንን ሁሉ የሚያደርገው የእረኞችን በር ከፍቶ እንስሳቶችን የሚያስወጣው እንደመምህር የለበሰው ሰው ማነው። እንደእኔ ጫጩት ጠፍቶት እሱ እየፈለገ ይሆን አለ። ምንአልባት ይሆናል የጠፉበትን ጫጩት ፍለጋ ይሆናል ወደዚህ የመጣው ብሎ አሰበ። መልኩን በይበልጥ ለማየት እና የት እንደሚያውቀው ለማስታወስ አትኩሩ ያየው እና ጆሮ ሰጥቶ ይሰማው ጀመር። ሰውዬው "እርሱም። ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው።"

የሉቃስ ወንጌል 19፥46

ነጋዴው እህ እህ መበለቷ ያለችኝ መምህር ይህ ነው እንደምንም ብዬ ለእሱ ሚስጢሩን እጠይቀዋለሁ።

ግን ቤቴ ማለቱ ወንበዴስ ማለቱ ምን ይሆን ግልጽ አልሆነልኝም ግን ይሄንንም ከአወቅኩት በኃላ መምህሩን የምጠይቀው ይሆናል። ውስጤን የሚረብሸኝ የአንድ ተራ ጫጩት ምክንያትን ሳያውቅ አይቀርም ንግግሩም ግርማውም ይሄንን ያስታውቃል ያለ አንዳች ምክንያት እዚህ አልተገኘሁም ያም ጫጩት ተራ አይደለም። ምን ይሁን ምን ብቻ ይህንን ሰው መምህሩን ጠይቄ ከተጫነብኝ ሸክም ነጻ እወጣለሁ። ይገርማል እኮ ሰው ቆይ እንዴት ለአንድ ጫጩት እንዲህ ይሆናል።

ቆይ እንዲህ የምሆነው ወላጆቼ ስለቃል ትልቅነት እና ኃያልነት ስላስተማሩኝ ይሆን እንዴ ለጫጩቱ ቃል ስለገባሁለት ይሆን? ምን አለ ቃል ባልገባለትስ ኖሮ አይ ግን። እያለ ብዙ አሰበ። ከአሳቡ ሲመለስ በዙሪያው ያሉ ሰዎች እያጉረመረሙ ነው። በማጉረምረም ውስጥ እና በትርምሱ መሃል በአይኑ መምህሩን ይፈልግ ጀመር ፈልጎ ፈልጎ ከቅጥሩ ሊወጣ ሲል አየው ማን ብሎ ይጥራው ጨነቀው እንደምንም ብሎ ሊደርስበት ተከተለው

አልቻለም አላገኘውም።

ነጋዴው ሰሞኑን ጥርጣሬ ውስጡ ገብቷል መምህሩን ፍለጋ አገኘዋለሁ ብሎ ቢፈልገውም አጥቶት ከአንድ ቦታ አረፍ ብሏል ለከተማው አዲስ ስለሆነ እና በእጂም ምንም አይነት የማደሪያ የሚችል ገንዘብ ስለሌለው በፊት በየቦታው ማደሩም ስለሰለቸው ቦታው ተስማምቶታል ወታደሮች ፣ ነጋዴዎች ፣ አመንዝሮች ፣ ጸሀፍት የሚሰበሰቡበት ቦታ ነበር በቦታው የማይገኝ ሰው ስለነበር የእኔ ነው የአንተ ነው የሚባል ነገር በስፍራው ስለሌለ ተመችቶታል እሱ ትንሽ ምቾት የነሳው ነገር መጀመሪያ ላይ ይጠይቁት የነበረው ጥያቄ ከየት መጣህ ስምህስ የማን ወገን ነህ እና መሰል ጥያቄዎች ነበሩ። መምህሩን ይፈልጋል ያገኘውን ይበላል ጸሎቱን አድርሶ ይተኛል ታዲያ ምሽቱ በጫጫታ ቢታወክም ተመሳሳይ ድምጽ ስለሚሰማ አይረብሸውም።

ዛሬ ተኝቶ ሳለ "አንቺ ሴት አላውቀውም" የሚል ድምጽ በጆሮው ሰሞ ቀጥለም ሰዎች ተናገር እያሉ ሲያሸካኩ ተመሳሳይ ድምጽ ሰው። አመላቸው ነው ብሎ ዝም አለ። ትንሽ ቆይቶ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ አንድ ሰዓት ቆይቶ ያው ድምጽ "አንተ ሰው እኔ አይደለሁም" ሲል ተሰማው አንቺ ሴት አላውቀውም? አንተ ሰው እኔ አይደለሁም? ግራ ገባው ማነው ደግሞ ይሄ ሰው አለ በውስጡ ከመኝታው ሳይነቃ። ነጋዴው የሚሆነውን ለማወቅ እና የሰውዬውን ማንነት ለመረዳት ሲል በመልክ ስለማያውቀው መልኩን ለማየት ድምጹን ለመስማት ከመኝታው ተነስቶ አካባቢውን ማየት ጀመረ ከፊቱ አንድ ሰውን አስረው ማነው ያሰረህ ብለው ያሰቃዩታል እሱ ይሆን እንደዛ ያለው ብሎ ድምጹን ለመስማት ቢፈልግም ምንም ምላሽ ሳይሰጣቸው ይገረፋል ጽናቱ ገረመው። ነጋዴው እንዲህ የው የሰው ህማም ይረዳል ፤ ቃሉን ይጠብቃል ፤ ትንሿን ነገር አግዝፎ ያያል ፤ ለሁሉም ጥያቄ መልስ ይሻል። "አንድ ሰዓትም የሚያህል ቆይቶ ሌላው አስረግጦ። እርሱ የገሊላ ሰው ነውና በእውነት ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ አለ።አንተ ሰው፥ የምትለውን አላውቅም አለ። ያን ጊዜም ገና ሲናገር ዶሮ ጮኸ።"

የሉቃስ ወንጌል 22፥59-60

ነጋዴው ድምጹን ሰምቶ ወደ ሰውዬው ሲዞር ሰውዬው ዓይኑ ላይ እንባ አቅሮ አየው አይቶት አያውቅም ግን አሳዘነው እንዲህ ነው ነጋዴ ሆደ ቡቡ። የሰውዬውን ዓይን ተከትሎ ሲያይ የገላሊው ሰው ላይ ዓይኑ መራው እሱን አየው ምንም አላለውም አንገቱን ወደ መሬት ሰበር አደረገ እንጂ። ቀድሞ ሊያውቀው ይፈልግ ወደነበረበት ሰውዬ ዓይኑን ሲልክ። ሰውዬው ሰዎችን ትቶ እያነባ በፍጥረት ከስፍራው ሲርቅ ታየው። ከፊት ለፊቱ የሚገረፈው ሰው ፊቱ በደም ተለውሶ ማንነቱ ጠፍቷል ሃሳቡ እሱ ላይ ነው እንቅልፍ አልወስድ አለው።

ለመተኛት ሲሞክር "አይገርምህም ይሄ ዶሮ አለው" ከጎኑ ተቀምጦ የነበረው ሰው። ነጋዴው ጭካኔአቸው አጸይፎት ሰምቶ እንዳልሰማ ለመሆን ሞከረ። አብሮት ያለው አዛውንቱ "አይገርምም ዛሬ ምን ታይቶት እንደጮኸ" ነጋዴው አልመለሰም ዝም። "የቀሬናው ስማኝ እንጂ እንደማትተኛ ውስጥህን የሚያስጨንቅህ ነገር ሁሌም እንዳለ አውቃለሁ ምን እንደሆን ባላውቅም የቀሬናው" ነጋዴው ዝም አለ። አብሮት ያለው አዛውንቱ ትንሽ ዝም ካለው በኃላ "ባይገርምህ እኔ እና ይሄ ዶሮ ስንመጣ ብዙ ሰውነበር ይሄ ምን አይነት ተዓምረኛ ዶሮ መሰለህ ከንጹህ እህል በቀር ፈጽሞ አይበላም ለዛውም ስንዴ ብቻ ነው የሚበላው ውሃ ራሱ ንፁህ ካልሆነ ፈጽሞ አይጠጣም ጠዋት ላይ ቤተ መቅደሱ ካሉ ሰዎች ጋር ሁሌም ግጭት ነው ውስጥ ዘው ብሎ እየገባ ይረብሻቸዋል መሰለኝ አስቸገረን እየገባ ይታረድ ይላሉ። በዛ ምክንያት ሁሌም እንጋጫለን የት እንደሚውል ራሱ አይታወቅም ማታ ላይ ነው እዚህ የሚመጣው እየው እስቲ" ነጋዴው ንግግሩ ቢያስገርመውም የገሊላው ሕማም እና ዝምታ ነብሱ ድረስ ስለተሰማው አልቅሼ ቢወጣልኝ ብሎ ሕመሙን እየታመ ነበር።

አዛውንቱ ንግግሩን ቀጠለ " ይገርምሃል እኔ ያገኘሁት አንድ መምህር በሚያስተምርበት ስፍራ ለምጽዋት ሄጄ እዛ ከመምህሩ እጅ የፈሰሱ ዘሮችን ሲበላ ነበር መምህሩ ያስተማረውን አልረሳውም ነበር። እንዲህ ነበር ያለው

'ዘሪ ሊዘራ ወጣ። እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት። ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው። ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።'የማቴዎስ ወንጌል13፥2-8 አላቸው። እሱ ካስተማረ በኃላ ከእጁ የተረፈውን ፍሬ በሙላ በላው የመምህሩ ዶሮ መስሎኝ አንስቼ ልሰጠው ስል አልሄድ አለኝ እኔም ወደዚህ ቦታ እንድመጣ የመራኝ እሱ ነው እሱን ተከትዬ አሁን ማን ያምናል እንደእኔ አይነቱ ትልቅ ሰው አንድ ትንሽ ጫጩት ተከትዬ እዚህ መጣ ብዬ ብናገር" ነጋዴው ጫጩት የሚለው ቃል ወደጆሮ ሲገባ ከመኝታው ተነስቶ "ጫጩት" አለ ለሰውዬው። "አዎን ምነው ደነገጥክ አንተም ይሄ ሰውዬ አርጅቷል የሚያወራውን አታውቅም ልትለኝ ነው?"

ነጋዴው እንደመደሰትም እንደማዘንም አይነት ስሜት ተሰማው። "እረ አይደለም ቆይ እንዴ እና ይሄን ጫጩት ከየት ነው የተገኘው" አዛውንቱ "ታሪኩ ብዙ ነው"። "ግዴ የለም ንገሩኝ ለመስማት ዝግጁ ነኝ" አለ ነጋዴው ጓግቶ "ይኸውልህ በቤተልሔም ከአንድ ማደሪያ ውስጥ ምስኪን ሰዎች አሳድረውኝ ነበር ታዲያ በዛ አንድ ቀን ከተጠለልኩ በኃላ በማለዳ ተነስቼ ለመሄድ ቆረጥኩ ሰዎቹ በቤታቸው የሚበላ ምግብ የላቸውም ነበር ግን እምነታቸው የሚያስገርም ነበር ለአምላካቸው ያላቸው ፍቅር ወደር የሌለው ነበር" ነጋዴው ወደጉዳዩ ቀጥታ ቢገቡ ደስ ባለው ነበር ነገር ግን አሁን የውስጡ ጥያቄ ምላሽ ስላገኘ ትንሽም ቢሆን ውስጡ ተስፋ ስላለ አዛውንቱን መስማትን መርጧል። አዛውንቱ ቀጥለው አንገታቸውን ሰበር አድርገው " ይገርምሃል ሰዎቹ አንዲት ዶሮ ነበረቻቸው ያቺ ዶሮን ነበር የሚጠብቁት እንቁላል አሳቅፈዋት በምትፈለፍላቸው ጫጩት ምክንያት ንስሃን እንደሚያገኙ ምህረት ወደቤታቸው እንደሚገባ ነበር የሚያምኑት ለእኔ ደግሞ በወቅቱ እንደዚህ አይነት ነገር ተራ የሕጻናት ጨዋታ ወይም ቀልድ ነበር የሚመስለኝ።

ሰውዬው ለባለቤቱ 'ይህች ዶሮ ልክ እንደእናቷ አንድ እንቁላል ብቻ ነው የጣለችው ካልፈለፈለችው ሂደቱን ማቆም ነው ግን እኛ ደግሞ አሁን ላይ ብትፈለፍል የምንሰጣት ምንም ነገር አይኖርም እንዴት ነው' አላት ለእኔ ጉዳዩ እንደህልም ይሰማኛል።" ነጋዴው "የምን ሂደት ነው?" ብሎ ጠየቀ። አዛውንቱ "እውነት ይሁን ቀልድ አንድ የሚነገር ታሪክ አለ ምን መሰለህ መሲሁ ሲወለድ በቤተልሔም ግርግም በትንፋሽ ካሞቁት እና ከተባረኩት እንስሶች መሃል በግ ፣ አህያ እና ዶሮ ይገኙበታል እና የእነሱ ዶሮም አንዷ እንደሆነች ነው የሚሰማቸው እናም ለዚህም ምክንያታቸው ደግሞ ሲያወሩ እንደሰማሁት ሰዎቹ ዶሮዎቹ በሙሉ አንድ እንቁላል ብቻ መጣላቸውን ነው የመጀመሪያዋ ዶሮ ልጇን ከፈለፈለች በኃላ ትንሽ ከፍ እንዳለች እንደምትጠፋ በምን አረጋገጥክ ብትለኝ 'ሚስትዬው ዶሮዋ ከፈለፈለች በኃላ ተለቅ እንዳለች ስለምትጠፋ ያን ያህል አታስብ ይሄ እንደሆነ የለመድነው ነገር ነው ችግር በእኛ ቤት ጠፍቶ አያውቅም አምላክ ይመስገን አትጨነቅ' ብላው ነበር። እና ያን የሰማሁትን ነገር በማለዳ ለማየት ጓግቼ ከበረት ያለ ፍቃዳቸው ገብቼ ከዶሮዋ ስር ሳይ እንዳሉትም አንድ እንቁላል ብቻ ነበር የነበረው። የዋህነታቸው አስገርሞኝ" አዛውንቱ ዝም አሉ። ነጋዴው "እሺ ከዛስ ምን ሆነ" ። አዛውንቱ እንባ እየተናነቃቸው "ከዛማ ለርሃቤ ማስታገሻ ይሆነኝ ዘንድ እበላው ዘንድ አስጎመጀኝ ሳልሰናበታቸው እኛን መልካም ምስኪን ሰዎች እንቁላል ለመብላት ራቤን ለማስታገስ ጉዞ ጀመርኩ። ግን" ነጋዴው ከሃሳብ እየራቁበት ወደጨጩቱ ሃሳብ እንዲመለሱ በመጓጓት "ግን ምን" ብሎ ጠየቀ "ግን መንገድ ብዙም ሳልጓዝ ደክሞኝ አረፍ ባልኩበት እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደኝ እና በሕልሜ"

አዛውንቱ ዝም አሉ። ነጋዴው አፋቸውን እያየ ቀጣይ የሚናገሩትን ይጠባበቅ ጀመር። አዛውንቱ ጉሮሯቸውን ጠራርገው "በሕልሜ አንዲት መበልት ሴት ምግብ ስትሰጠኝ እኔም ለእሷ ከቋጠሮዬ ውስጥ እንቁላሉን ቀይ ከላይ ለለበሰ ሰው ሰተሽ አንጅ ሳንቲም ሁለት ናሴ ተቀበይ ብዬ ስነግራት ታየኝ እና አንድ ሰው ይሄ የሕይወት መንገድ ነው የንስሃ የማንቂያ ደውል ሲለኝ ሰማው። ከእንቅፌ እንደነቃሁም ተነስቼ ትንሽ እንደተጓዝኩ በሕልሜ

ያየሁትን በእውኔ ስላገኘሁ። ሳላንገራግር አደረግኩት" ነጋዴው ፈገግ አለ። ይሄንን ጊዜ አዛውንቱ "አንተም እንደሌሎቹ አብደሃል አንተ ሽማግሌ ትለኝ ይሆናል ግን እኔ ጤነኛ ነኝ"።

ነጋዴው "እረ አይደለም ታሪኩ አስገርሞኝ ነው" አላቸው። ምላሹ እንደጠበቁት ስላልነበር ቀጠል አድርገው "አንተ የዚህ ከተማ ሰው ስላልሆንክ ሰውን ማክበር ትችልበታለህ የዚህ ሀገር ሰው ግን በእጅ ያለወርቅ ነው የሚያደርጉህ" አሉት ተከዝ ብለው። ነጋዴው "ይሄ የአብዛኞቻችን ጸባይ ነው ይልቅ ጨዋታውን ጨርሱልኝ ከዛ በኃላ እንዴት ሆኑ?" አዛውንቱ ተከዝ ብለው "ከዛ በኃላ ጉዳዩ ሕልሙ እሙን መሆኑ እውነት የተባለው ነገር ከትርክ ያለፈ እውነት ይሆን ወይ ብዬ በማሰብ የእንቁላሉን መጨረሻ ለማወቅ መበለቷ ቤት ሄጄ ለማን እንደሰጠችው ጠየኳት ለአንድ እንቁላል ነጋዴ አለቺኝ አዬ አልኳት ማዘኔን ስታይ ጊዜ 'ያልከኝን ሳንቲም ይኸው' አለቺኝ አለመፈለጌን ነገርኳት እሷም 'ለእግዚአብሔር ቤት እሰጣለሁ' አለቺኝ ጥሩ አደረግሽ እኔም መችስ በቤተልሔም ብዙ እንቁላል ነጋዴዎች የሉም ከሌላ ከተማ ካልመጡ በቀር ብዬ መርከብ ወዳለበት ሄድኩ" ትንሽ ረፍት ካደረጉ በኃላ "ግን እዛ ስደርስ ሰርክ ነበር እና ማንንም አላገኘውም ከሰዎች ልመጸወት እንዲረዱኝ ወደተሰባሰቡበት ሲሄድ ሄንን ጫጩት ከመምህሩ የተረፈውን ሲበላ ያገኘሁት" ነጋዴው ይሄንን ሲሰማ ከመቅጽፈት ተነስቶ ከመኝታው በጉልበቱ ተደፍቶ አመሰገነ።

አዛውንቱ እስኪነሳ ጠበቁት እና "ምን ሆነህ ነው እንዲህ የምትሆነው" አሉት። ነጋዴው "ጫጩቴ ተገኘ አለ" አዛውንቱ ግራ ተጋቡተው "የምን ጫጩት?" ጠየቁት " ነጋዴው "የምስኪኖቹ ሰዎች እንቁላል ለመበልቷ የሰጧት ቀይ ከላይ የለበስኩት የእንቁላል ነጋዴ እኔ ነኝ" አዛውንት ተገርመው "ምን አልከኝ እኔ ነኝ?"። ነጋዴው በደስታ እየተፍከነከነ "እኔ ነኝ ነጋዴው ዶሮ ደግሞ ይኸው " አዛውንቱ እያመነቱ "እንደዛ እንዴት ይሆናል ሰዎቹ ሁሉም ዶሮች የሚወልዱት ሴት ነው ብለው ነበር እንዴት ይሄ ሊሆን ቻለ ወይ አንተ ወይ እኔ ተሳስተናል"። ነጋዴው "አይመስለኝም ማናችንም አልተሳሳትንም ጫጩቱ ይሄ ነው ቆይ ከዚህ በፊት ዶሮው ጮኾ ያውቃል?" ብሎ ጠየቃቸው። አዛውንቱ "አረ በፍፁም"። ነጋዴው በደስታ "እኔም ውስጤ ቅልል አለው ግን ይሄ ሁላ ወራት ይሄንን ሚስጢር ብቻ ለማወቅ ነው ይገርማል ይሁን መችስ" አለ። አዛውንቱ ይሄንን ጊዜ ደንገጥ ብለው አካባቢያቸውን መቃኘት ጀመሩ። ነጋዴው በሁኔታቸው ግራ ተጋብቶ "ምነው ምን ሆነው ነው አላመኑኝም እንዴ? እ"

አዛውንቱ "እረ አይደለም ከዛፉ ስር ተኝቼ የታየኝ ሕልም ላይ አንዴ ታገኘኛለህ ግን አትረዳኝም ለሆድህ ታስበኛለህ ግን ድምጹን ስትሰማ ከፊት ነኝ እና ማረኝ ብቻ በለኝ እኔ እምሃለው የሚል ድምጽ ሰምቼ ነበር አሁን ስረዳው" አሉት። ነጋዴው ግራ ተጋብቶ "አልገባኝም ምንድነው?" አዛውንቱ ፊታቸው እየወዛ ዓይናቸው እየደፈረሰ በእንባ እየተሞላ "እየፈለግኩት ነው የት ይሆን ያለው ከፊቴ አቤቱ የት ነው ያለኸው የምትምረኝ።" ብለው ተንበርክከው መፈለግ ጀመሩ። ነጋዴ ግራ ተጋብቶ የሚሆነውን ማየት ጀመረ። ይሄንን ጊዜ የወታደሮቹ አለቃ ይገርፉት የነበሩትን ሰዎች ይበቃል አላቸው። ከወታደሮቹ መሃል አንዱ የገሊላው ሰው ላይ ያለውን ደም ሲጠርግ። አዛውንቶ ዓይናቸው እንባን እያመነጨ "አቤቱ በደለኛውን ማረኝ ይቅር በለኝ" ብለው ስቅስቅ ብለው አለቀሱ።

ነጋዴው ወደገሊላው ሰው ሲያይ ያ ግርማው የሚያስፈራው መምህር መሆኑን ተረዳ ፊቱ በመጸፋት ምክንያት በመቀጥቀጥ ብዛት ቢወረዛም ገጹ ላይ ግን አሁንም ግርማው አለ። ከአዛውንቱ ስሜትን ተጋርቶ እንባን ሳይበደር ሳያስበው የዓይኖቹ ጉድጓዶች በእንባ ተሞሉ ከየት መጣ ያላለው ትኩስ እንባ በግራ እና በቀኝ ጉንጩ መሃል ቁልቁል ወረደ። ምንም አላለም አልተናገረም አዛውንቱንም ባሉበት እዛው ትቷቸው የገሊላውን ሰው ተከተለው። ነብሱ በፍቅሩ እሳት ነደደች የጌታችን የአምላካችን የንጉሣችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅሩ ስሙን ሲሰማ መሲው በውስጡ ብሎ ሳይሰስት ሳያስበው ውስጡ የገነፈለው ስሜት በእንባው ብቻ ይገለጽ ጀመር ለአፍታ ሳያቆም እያነባ እስከ ከጲላጦስ የፍርድ አደባባይ ድረስ ደረሰ። ይሰቀል ሲባል በፍቅሩ ተሰቀለ።

የአሌክስንድሮስና የሩፎስን አባት። ከራሱ ጋር ተጋጭቶ ከልብ ተጣልቶ ጥቂቲ ወደገጠር ተጉዞ መርከብ ይዞ ሊሄድ ወሰነ ግን በቃ አልቻለም ፍቅሩ በርትቶበታል እና ተመለሰ

ያ ለአንድ ጫጩት ብሎ ለወራት የተንከራተተ በብዙ እንቁላሎች ዋጋ ለመበልት አዝኖ በአንድ ሳንቲም በሁለት ናስ የገዛት አንድ እንቁላል የገዛት ለአዛውንት ጆሮ የሚሰጥ ምስኪን ነገዴ። ፍቅሩ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትም ነበር እና የድንግል ማርያም ልጅ ጌታችን አምላካችን ንጉሣችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን " አንድ መንገድ አላፊም የአሌክስንድሮስና የሩፎስ አባት ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።"

የማርቆስ ወንጌል 15፥21

አይሁድ ያስገደዱት የመሰላቸው እርሱ ግን በፍቅሩ የጌታን መስቀል የተሸከመ ለቃሉ በመታመኑ የጌታን መስቀል የተሸከመ ሰው ሆነ።

ተጻፈ፦ ኢዩኤል ሰለሞን (ኢሰረያ)

ዕለተ እሁድ ጠዋት 4:25 ሚያዝያ 27/2016ዓ.ም

እውነታ 30% ግላዊ ምልከታ 40 ፈጠራ 30